ABCON – Research & Consulting
Social, marketing & opinion researchers

AFRO BAROMETER 1999-2019
20 years of giving voice to Africans

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
ነሐሴ 19 2012 ዓ.ም

# ከጥናቱ ግኝቶች ፕሬስ ሪሊዝ

## ኢትዮጵያውያን የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግስት እንዲሻሻል፣ የፌደራል የስራ ቋንቋ ከአማርኛ በተጨማሪ ሌሎች እንዲታከሉ፣ የጠቅላይ ሚንስቴር የስልጣን ዘመን እንዲገደብ ሲስማሙ በሌሎቹ መመዘኛዎች ላይ ልዩነት አሳይተዋል፡፡

ኢትዮጵያውያን የሀገራቸው ህገ-መንግስት እንዲሻሻል፣ የፌደራል መንግስቱ የስራ ቋንቋ እንዲበዛ እና የጠቅላይ ሚንስትሩ የስልጣን ዘመን እንዲገደብ እንደሚፈልጉ አዲሱ የአፍሮ ባሮሜትር የጥናት ውጤት አመላክቷል፡፡ ሆኖም የመሬት ባለቤትነትን ለዜጎች ስለመስጠት፣ ራስን-በራስ የማስተዳደር መብት፣ የሕገ-መንግሥት ፍርድ ቤት ስለማቋቋም፣ በሀገሪቷ ባንዲራ መሐል ላይ ያለው አርማ በተመለከተና በአዲስ አበባ ከተማ የአስተዳደር ሁኔታ ላይ የጥናቱ ተሳታፊዎች አስተያየት የተከፋፈለ ነበር፡፡

አብዛኞቹ የጥናቱ ተሳታፊዎች የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ-መንግስት መሻሻል እንጂ በአዲስ መተካትና እንደነበረው መቀጠል እንደሌለበት ይስማማሉ፡፡ ይህም በሀገሪቷ ዛሬ ላይ ያሉትን ፍላጎቶች ለማስታረቅና ለማካተት እንደሚያግዝ ጠቁመዋል፡፡ ይህ እንዳለ ሆኖ ህገ-መንግስቱ በሚሻሻልበት ወቅት የተርታው ህብረተሰብ ሀሳብና ተሳትፎ ሊኖረው ይገባል ብለዋል፡፡

አብላጫዎቹ የጥናቱ ተሳታፊዎች እንዲሁ የፌደራል መንግስቱ የስራ ቋንቋ ከአማርኛ በተጨማሪ ሌሎች ቋንቋዎች እንዲካተቱ፣ የሀገሪቷ ጠቅላይ ሚኒስትር ስልጣን በሁለት የምርጫ ጊዜ ብቻ እንዲገደብና ከፌዴሬሽን ምክር ቤት ውጪ የሕገ-መንግስት ጉዳዮችን የሚያይ ፍርድ-ቤት እንዲቋቋም ይሻሉ፡፡

የጥናቱ ውጤት እንደሚያሳየው በሀገሪቷ የፖለቲካ ልሂቃን መካከል አወዛጋቢ በሆኑ የህገ-መንግስቱ አንቀፅ እንዲሻሻል ለጥናቱ ተሳታፊዎች ጥያቄ ቀርቦላቸው፤ ጠንከር ያለ ድጋፍና ተቃውሞ ለማየት ተችሏል፡፡ ከእነዚህ ውስጥ ዋነኞቹ አንቀፅ 39 ማለትም የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ራስን በራስ ማስተዳደር እስከ መገንጠል፣ የመሬት ባለቤትነት ከመንግስትና ህዝቦች ወደ ዜጎች መቀየር እና በሀገሪቷ ሰንደቅ ዓላማ መሐል ላይ ያለው አርማ ይወገድ የሚሉት ናቸው፡፡

ከለውጡ በኋላ በሀገሪቷ በተከፈተው የፖለቲካ ምህዳር መሰረት የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግስትን በተመለከተ እየተደረጉ ላሉ ክርክሮች የሚሆኑ አጋዥ መረጃዎች ከጥናቱ ውጤት ተገኝቷል፡፡ ባለፉት ሁለት ዓመታት ከሀገር ውጪ የነበሩ ተፎካካሪ ፓርቲዎች ወደ ሀገር መግባትን ተከትሎ ህገ-መንግስቱ እንዲሻሻል የተለያዩ ድምፆች ይሰማሉ፡፡ በሀገሪቷ በታየው ለውጥ እንዲሁ ሚዲያዎች ተስፋፍተዋል፡፡ በኢ..ፌ.ዴ.ሪ ህገ-መንግስት ላይ በተለያዩ አካላት የሚታዩ ልዩነቶችን ለማስታረቅ ሚዲያዎች የፖለቲካ ምሁራንን በመጋበዝ ጠንከር ያሉ ክርክርና ሙግቶች እየፈጠሩ ይገኛሉ፡፡

Copyright ©Afrobarometer 2020

## የጥናቱ ዋና ዋና ግኝቶች፤

- በጥናቱ ከተሳተፉ 10 ኢትዮጵያውያን ሰባቱ (ማለትም 69 በመቶዎቹ) የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ-መንግስት እንዲሻሻል ይፈልጋሉ፤ ከ11 በመቶዎቹ ከነአካቴው መወገድ ወይም በአዲስ መተካት አለበት ሲሉ፤ 18 በመቶዎቹ ደግሞ ህገ-መንግስቱ አሁን ባለበት እንዲቀጥል ይሻሉ። (ለዝርዝሩ ግራፍ አንድን ይመልከቱ)

- አብዛኛዎቹ የጥናቱ ተሳታፊዎች በህገ-መንግስቱ ካሉ አንቀፆች እንዲሻሻል የሚፈልጉት የሚከተሉት ናቸው። (ግራፍ 2)

    - በፌዴራል መንግሥት ተጨማሪ የሥራ ቋንቋዎች ማካተት (73 በመቶ)
    - ጠቅላይ ሚኒስትር ለሁለት የምርጫ ጊዜ ብቻ እንዲያገለግል ማድረግ (73 በመቶ)
    - ሕገ መንግሥቱን የመተርጎም ስልጣን የተሰጠው ለፌዴሬሽን ምክር ቤት ነው። ከምክር ቤቱ ውጪ የሕገ-መንግስት ጉዳዮችን የሚከታተል ፍርድ ቤት ማቋቋም ናቸው።

- ሌሎቹ መመዘኛዎች ላይ ህገ-መንግስቱ ቢሻሻል ያሉ አናሳ ድርሻ ይዘዋል።

    - ከ10ሩ የጥናቱ ተሳታፊዎች አራቱ ኢትዮጵያውያን (በሌላ አነጋገር 43 በመቶዎቹ) አንቀፅ-39 ከህገ-መንግስቱ እንዲወጣ ጠቁመዋል። አንቀፅ 39 የብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች የራስን ዕድል በራስ የመወሰን እስከ መገንጠል ዋስትና የሚሰጥ እንዲሁም የራስን ክልል የማዋቀር መብት የሚያረጋግጥ በመሆኑ በህገ-መንግስቱ እንዲቆይ ያሉ 50 በመቶ ድርሻ ይዘዋል።
    - የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ-መንግስት የመሬት ባለቤትነትን ለመንግስትና ለህዝብ ይሰጣል። ይህ የባለቤትነት መብት ለዜጎች ቢሰጥ የሚል ጥያቄ ቀርቦ ተቀራራቢ ድርሻ ያላቸው የጥናቱ ተሳታፊዎች በድጋፍና በተቃውሞ ምላሻቸውን ሰጥተዋል። በቅደምተከተል 49 በመቶና 46 በመቶ ድርሻ አላቸው።
    - ከ10ሩ የጥናቱ ተሳታፊዎች ከአራት የሚያንሱ ኢትዮጵያውያን (ማለትም 37 በመቶዎቹ) በብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማው መሃል ላይ ያለው አርማ እንዲጠፋ ሲፈልጉ፤ ከግማሽ በመቶ ብልጫ የሚይዙት ደግሞ እንዳለ ቢቆይ ይመርጣሉ።
    - 1/3 የሚሆኑት የጥናቱ ተሳታፊዎች አዲስ አበባ ራሷን የቻለች ክልል ብትሆን ሲመርጡ፤ ከግማሽ በመቶ የሚበልጡት (ማለትም 54 በመቶዎቹ) ደግሞ ይህን ሃሳብ ይቃወማሉ።

- ኢትዮጵያውያን የኢ.ፌዴ.ሪ ህገመንግስት መቼ ይሻሻል የሚለው ሀሳብ ላይ የተለያየ አቋም እንዳላቸው የጥናቱ ውጤት ያሳያል። ከጥናቱ ተሳታፊዎች 1/3ኛ የሚሆኑት የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ-መንግስት ከ6ኛው ሀገራዊ ምርጫ አስቀድሞ ቢሻሻል ሲሉ፤ ተመሳሳይ ድርሻ ያላቸው (ማለትም 33 በመቶዎቹ) ደግሞ ምርጫው ተካሂዶ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ቢሻሻል ሲሉ፤ ቀሪዎቹ 29 በመቶዎቹ ምርጫው ከተካሄደ ከአንድ ዓመት በኋላ ቢሻሻል ይመርጣሉ። (ለዝርዝሩ ግራፍ ሶስትን ይመልከቱ)

- በጣም ከፍተኛ ድርሻ ያላቸው የጥናቱ ተሳታፊ ኢትዮጵያዊያን (ማለትም 92 በመቶዎቹ) የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ-መንግስት የማሻሻል ሂደት ሲደረግ ተርታው ማህበረሰብን ባሳተፈ መልኩ መሆን እንዳለበት

ገልፀዋል። ከ7 በመቶ የሚበልጡት ደግሞ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ-መንግስት ሲሻሻል በምርጫ የተመረጡ የፖለቲካ አመራሮችን ባሳተፈ መልኩ እንዲሆን ጠቁመዋል (ምስል 4)።

## የአፍሮ-ባሮሜትር ጥናቶች

አፍሮ ባሮ-ሜትር አፍሪካ ላይ ትኩረት ያደረገ ገለልተኛ የሆኑ የጥናትና ምርምር ስራዎችን የሚሰራ ተቋም ነው። ይህ ተቋም ታማኝ የሆኑ መረጃዎችን በዋናነት ዲሞክራሲ፣ አስተዳደርና የኑሮ ጥራት ላይ በማሰባሰብ የካበተ ልምድ አፍርቷል። ተቋሙ ሰባት ዙር ጥናቶችን በ38 ሀገራት ላይ ከ1999 እስከ 2018 እ.ኤ.አ መስራት የቻለ ነው፡፡ ስምንተኛ ዙር ጥናት በ2019/2020 የተካሄደ ሲሆን፤ ከ35 ሀገራት በላይ ተሳትፈውበታል። የአፍሮ ባሮ-ሜትር ጥናቶች የሚያካሄዱት በዋናነት በገፅ-ለገፅ ቃለ-መጠይቅ ሲሆን፤ የጥናቱ መረጃ አሰባሰብ ሂደት የጥናቱ ተሳታፊዎች በመረጡት አካባቢያዊ ቋንቋ ይሆናል። ጥናቱ የሚካሄደው ወካይ የሆነ የናሙና መጠን በመመደብ ነው።

በፍሪደም ሀውስ ድጋፍ የኢትዮጵያ አፍሮ ባሮ-ሜትር ቡድን የተመራው በአብከን-የአማካሪ ድርጅት ነው። ጥናቱ የተካሄደው 2400 ቃለ-መጠይቆችን ዕድሜአቸው 18ና ከዚያ በላይ የሆኑ ኢትዮጵያዊያን በማሳተፍ፤ መረጃው ከታህሳስ እስከ ጥር 2020 እ.ኤ.አ ተሰባስቧል። የናሙናው መጠን በሀገር አቀፍ ደረጃ የተሰራና ወካይነት ያለው ሲሆን፤ የስህተት ህዳጉ +/-2 መቶኛና የአስተማማኝነት ደረጃው 95 በመቶ ነው። የአፍሮ ባሮ-ሜትር ጥናት ከዚህ ቀደም በኢትዮጵያ የተካሄደው በ2013 እ.ኤ.አ ነበር።

## የግራፎች ዝርዝር

**ግራፍ 1፡ የኢትዮጵያ ህገ-መንግስት አሁን እንዳለው ቢቀጥል ወይስ ቢሻሻል ወይስ በአዲስ ቢተካ ይላሉ?** | ኢትዮጵያ | 2020




**ለጥናቱ ተሳታፊዎች ቀርበላቸው የነበረው ጥያቄ፤** ከሚከተሉት ሶስት አስተያየቶች/ሀሳቦች የትኛው ከእርስዎ አስተያየት/ ሀሳብ ጋር የተቀራረበ ነው?

Copyright ©Afrobarometer 2020

ሀሳብ 1: አሁን ያለው ህገመንግስት እንዳለ መተው አለበት፤ ማሻሻል ወይም ሪፎርም ማድረግ አያስፈልግም።
ሀሳብ 2: አሁን ያለው ህገመንግስት እንዳለ ሆኖ ከወቅቱ ሁኔታና ፍላጎት ጋር እንዲጣጣም ማሻሻያ ሊደረግበት ይገባል።
ሀሳብ 3: አሁን ያለው ህገመንግስት እንዳለ ተወግዶ/ተጥሎ በአዲስ ህገመንግስት መተካት አለበት።

**ግራፍ 2: የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ-መንግስት እንዲሻሻል ይፈልጋሉ ወይስ አይፈልጉም?** | ኢትዮጵያ | 2020




## ለጥናቱ ተሳታፊዎች ቀርቦላቸው የነበረው ጥያቄ፤

አሁን ያለውን የኢትዮጵያ ህገመንግስት በተመለከተ እንዴት የተወሰኑ የህገመንግስቱ አንቀጾች መሻሻል ወይም መቀየር እንዳለባቸው የተለያዩ ሀሳቦች ይሰጣሉ። በኢትዮጵያ ህገመንግስት ላይ መሻሻል ወይም መቀየር አለባቸው የተባሉትን የሚከተሉትን አስተያየቶች/ሀሳቦች ይደገፋሉ ወይስ ይቃወማሉ ወይስ ኣስተያየት ለመስጠት በጉዳዩ ላይ በቂ እውቀት የለዎትም?

- አንቀጽ 39፣ የብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦችን የራስን ዕድል በራስ መወሰን ማብት እስከመገንጠልና የራሳቸውን ነጻ መንግስት መመስረት የሚለው አንቀጽ መዉጣት/መሰረዝ ኣለበት።
- ዜጎች የመሬት ባለቤትነት መብት እንዲኖራቸው መሬት ሁሉ በመንግስት ባለቤትነት መያዝ እንዳለበት የሚያረጋግጠው ኣንቀጽ መለወጥ ወይም መሰረዝ አለበት።

- በኢትዮጵያ ባንዲራ ላይ መኖር ስለአxለበት ምልክት የሚገልጸዉ አንቀጽ መለወጥ ወይም መሰረዝ አለበት።
- ከአማሪኛ በተጨማሪ ሌሎች ቋንቋዎችም የፌዴራል መንግስት የስራ ቋንቋ መደረግ አለባቸው።
- ከፌዴሬሽን ምክር ቤት የተለየ የህገመንግስት ፍርድ ቤት ማቋቋምን የሚወስን አንቀጽ መጨመር አለበት።
- አዲስ ኣበባን ወደ ፌዴሬሽን ምክር ቤት  አባልነት ከፍ መደረግ እንዳለበት የሚወስን አንቀጽ መጨመር አለበት።

ከሚከተሉት አስተያየቶች/ሀሳቦች የትኛው ከእርስዎ አስተያየት/ ሀሳብ ጋር የተቀራረበ ነው?

ሀሳብ 1፡ ህገ-መንግስቱ የጠቅላይ ሚንስትርን የስልጣን ዘመን ሁለት የምርጫ ጊዜ ብቻ እንዲሆን መገደብ አለበት

ሀሳብ 2፡ በህገ-መንግስቱ ላይ የጠቅላይ ሚንስትርን የስልጣን ዘመን የሚገድብ አንቀፅ መኖር የለበትም

**ግራፍ 3፡ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ-መንግስት መቼ ይሻሻል? | የጥናቱ ውጤት በከተማ-ገጠር ነዋሪነት |** ኢትዮጵያ | 2020




**ለጥናቱ ተሳታፊዎች ቀርቦላቸው የነበረው ጥያቄ፤** ህገመንግስቱ መሻሻል ወይም መለወጥ ካለበት የማሻሻሉ ወይም የመለወጡ ሥራ መቼ መሰራት አለበት ብለው ያስባሉ?

Copyright ©Afrobarometer 2020 

**ግራፍ 4፡ ህገመንግስቱን ለማሻሻል ወይም ለመለወጥ የህገመንግስት ግምገማ ሲካሄድ ተራው ህብረተሰብ መካፈል አለበት ወይስ የተመረጡ የፖለቲካ መሪዎች ሥራና ተግባር ነው ይላሉ?** | ኢትዮጵያ | 2020




**ለጥናቱ ተሳታፊዎች ቀርቦላቸው የነበረው ጥያቄ፤** ከሚከተሉት አስተያየቶች/ሀሳቦች የትኛው ከእርስዎ አስተያየት/ ሀሳብ ጋር የተቀራረበ ነው?

> ሀሳብ 1፡ ህገመንግስቱን ለማሻሻል ወይም ለመለወጥ የህገመንግስት ግምገማ ሲካሄድ ተራውን ህብረተሰብም ማወያየት ያስፈልጋል።
>
> ሀሳብ 2፡ ህገመንግስቱን ማሻሻል ወይም መለወጥ የተመረጡ የፖለቲካ መሪዎች ሥራና ተግባር ነው፤ ተራውን ህብረተሰብ ማወያየት ኣስፈልግም።

(የመቶኛ ድርሻው ለሁለቱም ሀሳቦች "እስማማለሁ" ወይም "በጣም እስማማለሁ" ያሉትን ይይዛል)

## For more information, please contact:

Mulu Teka
National Investigator
ABCON – Research & Consulting
Tel +251 973 077 414 , +251 115 531 470, +251 115 521 696, +251 115 537 061
mulu.mtg@gmail.com / info@abconltd.et
Addis Ababa, Ethiopia

Visit us online at:
www.abconltd.et
www.afrobarometer.org

Follow our releases on #Voices Africa.

/Afrobarometer @Afrobarometer

Copyright ©Afrobarometer 2020